ጁን 8ቀን 2020ዓ.ም.

Fairfax County የህዝብ ት/ቤቶች የርቀት ትምህርት የእቅዱ አካል ሆኖ በተራዘመው የትምህርት ዓመት (ESY) ውስጥ የትምህርት ጥቅሎች /እቅዶች  እየሰጡ ናቸው፡፡ በጥቅሉ/በእሽጉ ውስጥ ያሉት ተግባራት የተማሪዎችን የመሳተፍ እና የአስተሳሰብ ፍላጎቶች ሲደግፉ ተማሪዎች ክህሎቶችን እንዲለማመዱ እና ተግባራዊ እንዲያደርጉ እድል ይሰጣቸዋል። በአራቱ ሳምንታት ESY ውስጥ ቤተሰቦች የትምህርት ጥቅሎችን/እሽጎችን ወደ ቤታቸው እንሚላኩ እና በጥቁር ሰሌዳ ላይ እንደሚለጠፉ ይጠብቁ፡፡ እባክዎን እነዚህን መርጃዎች ይጠቀሙባቸው፡፡

ጽሑፎቹ በESY ለተካተቱ ተማሪዎች **የማንበብ ችሎታን** ፣ **መተርጎምን** ጨምሮች **ቃላትን** ፣ **መረዳትን** እና **አጻጻፍን** እንዲሁም **የሂሳብ** ክህሎት እና **የቀመር** እና **ችግር መፍታትን** የሚያካትቱ የትምህርት እንቅስቃሴዎችን ይዘዋል። በተጨማሪም የ ESY ትምህርት አከባቢን ፣ መርሃግብሮችን ፣ ማጠናከሪያዎችን ፣ ራስን መቆጣጠር እና ማህበራዊ ክህሎቶችን ለማዘጋጀት እርምጃዎችን ጨምሮ ተግባራዊ ባህሪይ ስልቶችን ያገኛሉ ፡፡ እነዚህ ጥቅሎች/እሽጎች በመምህር የሚሰጥ ትምህርትን እና በኢንተርኔት አማካኝነት የሚሰጥ የትምህርት መርሃግብርን ለማጣጣት የተዘጋጁ ናቸው፡፡ ወላጆች እነዚህን ጥቅሎች እየለዋወጡ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። እባክዎ ተገቢዎቹን እንቅስቃሴዎች እና ጥያቄዎች በተመለከተ ከልጅዎ መምህር ጋር አብረው ይስሩ።  ምንም እንኳን እነዚህ ተግባራት የተማሪን በግል የሚካሄድ ትምህርት ለመደገፍ የታቀዱ ቢሆኑም ፣ ተማሪዎች ጮክ ብለው ማንበብ ወይም እንደ ሃሳባቸውን በቃል መግለጽ ያሉ አገልግሎቶችን በማመቻቸት መጠቀም ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም አንዳንድ እንቅስቃሴዎች ከባልደረባ ጋር አብሮ መስራትን ያካትታሉ ይህ ሲሆን ተማሪዎች ከቤተሰብ አባል ጋር መስራትን ይችላሉ።